# ከቅዠት ውጡ

ፊሊጶስ /ከካዛንችስ/

ተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲ መሪዎች ከ85 በመቶ በላይ የሚሆነውን የኢትዮጵያ አርሶ አደር መሬት እንዲሸጥ እንዲለወጥ አደርጋለሁና ምረጡኝ የሚል አቋም እንደአማራጭ አቅርበውለት ለሥልጣን እንዲያበቃቸው ነበር የምርጫ ቅስቀሳቸውን ሲያካሂዱ የነበሩት፡፡ ይህም ከአንድ ሄክታር ባልበለጠ መሬት ላይ ኑሮውን የመሠረተውን፣ ከግብርና ውጪ መተዳደር የሚያስችለው ሌላ ተያያዥ ሙያ የሌለውን፣ በይዞታው ሥር ያለችውን መሬት ቢሸጥና ቢፈናቀል ሌላ ምንም የኑሮ አማራጭ የሌለውን ብዙሀኑን አርሶ አደር ህይወት የሚታደግ ሳይሆን ወደ አዘቅት የሚከት የመከራከሪያ ነጥብ ነበር፡፡

ተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎች በተለይ በመሬት ጉዳይ ላይ ለያዙት አቋም ያስረዳልኛል ያሉትን መከራከሪያ ሁሉ አቅርበዋል፡፡ ‹‹አርሶ አደሩ መሬቱን የመሸጥ የመለወጥ መብቱ ተከበረለት ማለት እንዲሸጥ ይገደዳል ማለት አይደለም፤ ክልከላው አርሶ አደሩ መሬቱን ሸጦ በሌላ ሥራ ላይ መሰማራት ቢፈልግ ይህን መብቱን አሳጥቶታል›› የሚለው አንዱ የመከራከሪያቸው ነጥባቸው ነበር፡፡

ተቃዋሚዎች በሰፋፊ እርሻ ኢንቨስትመንት ላይ መሰማራት ለሚፈልጉ ባለሀብቶች የመሬት አቅርቦት ዕድልን ይፈጥራል፣ ብጥስጣሽ እርሻ ያስከተለውን የምርታማነት ችግር ያቃልላል የሚል መከራከሪያ ነጥብም ነበራቸው፡፡

*የሀገራችን ተጨባጭ እውነታ ግን ፍፁም ከዚህ የተለየ ነው፡፡ ቀደም ሲል በተቃዋሚዎች የተገለፀውን የአርሶ አደሩን የኑሮ ሁኔታ ግምት ውስጥ ብናስገባ እንኳ መሬቱን ሸጦ በሌላ አካባቢ በተለየ ሙያ ላይ በመሰማራት መኖር የሚችልና የሚፈልግ አርሶ አደር ቢሆን እንኳን፣ መሬቱን መሸጥ ሳያስፈልገው እንደሁኔታው በሚታደስ ውል እስከ30 ዓመት ለሚደርስ ጊዜ መሬቱን ለማከራየት የሚያስችል የመሬት ፖሊሲ ተቀርፆ በሥራ ላይ እንዲውል ተደርጓል፡፡*

*‹‹ሰፋፊ የእርሻ መሬት አቅርቦትን መፍጠርና የብጥስጣሽ እርሻን ችግር ማቃለል የሚለው የተቃዋሚዎች መከራከሪያም፣ ሊያስተዳድሩት የሚፈልጉት አገር ላይ ያለውን፣ ማንም በቀላሉ ሊያውቀው የሚችለውን እውነታ ካለመገንዘብ የመነጨ መሠረታዊ ስህተት ነው፡፡ እኔ እንደሚመስለኝ በቅድሚያ በአርሶ አደሩ ይዞታ ስር ያለ በሺዎች ሄክታር የሚለካ ለሰፋፊ እርሻ ልማት የሚውል መሬት በግዥ ለማግኘት፣ በመቶዎችና በሺዎች የሚቆጠሩ ኩታ ገጠም መሬት ያላቸው አርሶ አደሮች በተመሳሳይ ጊዜ መሬታቸውን የመሸጥ ተመሳሳይ ፍላጎት እንዲኖራቸው የግድ የሚል ይሆናል፡፡*

*ይህ በሆነ ታምራዊ ኃይል ካልሆነ በስተቀር በየራሳቸው ጎጆ፣ በየራሳቸው ስሜት/ሥነልቦናዊ ሁኔታ/፣ ፍላጎት፣ ራዕይ... ህይወታቸውን የሚመሩ ሚሊዬን አርሶአደሮች ይዞታቸውን ዳግም ላያገኙት፤ በማያውቁት አካባቢ፣ በማያውቁትና ሙያውና ልምዱ በሌላቸው የሥራ መስክ ላይ ተሰማርተው የራሳቸውንና የቤተሰቦቻቸውን ኑሮ ለዘለቄታው መምራት የሚያስችል አቅም ይኖራቸዋል ብሎ መገመት ከጠቅላላ ህዝቡ 85 በመቶ የሚሆነውን ለማሞኘት የተደረገ ቂልነት ነው፡፡*

ከዚህ በተጨማሪ አገሪቱ ካላት ለእርሻ ተስማሚ ከሆነው ለም መሬት መካከል፣ እስካሁን የለማው አሥራ አምስት በመቶ እንኳን አይሞላም፡፡ በሀገሪቱ በሰፋፊ እርሻ ላይ መሰማራት የሚፈልጉ ባለሀብቶች መሬት በተመጣጣኝ የሊዝ ዋጋ ማግኘትና ማልማት የሚችሉበት ሰፊ እድል የተፈጠረ በመሆኑ ባለሀብቶች ይህን እድል ሊጠቀሙበት፤ ተቃዋሚዎችም ይህን መሠረታዊ እውነት ሊረዱት ይገባል፡፡

ሌላው ነጥብ ተቃዋሚ ፓርቲዎቹ በመሠረታዊ የህገመንግሥቱ አንቀጾች ላይ የሚያቀርቡት ተቃውሞ ነው፡፡ ይህም የህገመንግሥቱ መነሻ የሆነውን የአገሪቱን ነባራዊ ሁኔታ ካለመገንዘብ፣ አሊያም በጭፍን ተቃውሞ እና በጥላቻ ፖለቲካ የተጋረደ የሥርዓት ለውጥ ለማምጣትና አገሪቷን ወደቀደምቱ የአምባገነኑ ሥርዓት ለመመለስ ካለ ፍላጎት የመነጨ ፀረ ዲሞክራሲያዊ አቋም ነው፡፡

ለዚህም በ1997 ምርጫ ላይ ዋነኛ ተፎካካሪ ሆነው የቀረቡት የኢትዮጵያ ዴሞክራሲ ኃይሎች ህብረትና የቀድሞው ቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ ከዚያ በፊት ታይቶ በማይታወቅ ሁኔታ የተሻለ የክልልና የፌዴራል ም/ቤቶች መቀመጫ ማግኘት ቢችሉም፣ የተሰጣቸውን የህዝብ ውክልና መቀበል አለመፈለጋቸውና ከህዝብ ያፈነገጠ አቋም መያዛቸው፤ ህገመንግሥታዊ ባልሆነ መንገድ የመንግሥት ሥርዓት ለውጥ ለማምጣት ያላቸውን ፅኑ ፍላጎት ይመለከታል፡፡ እንዲሁም ህብረት በመጨረሻው ሰዓት ላይ አዝማሚያውን አይቶ እንደማያዛልቀው ሲረዳ አቋሙን ቀይሮ ወደ ህዝብ ተወካዮች ም/ቤት ቢገባም፣ በተለይ አዲስ አበባን ሙሉ በሙሉ የማስተዳደር የህዝብን ውክልና አግኝቶ የነበረው የቀድሞው ቅንጅት ይህን ከማድረግ ይልቅ የመረጠውን ህዝብ ድምፅ በአመፅ መሣሪያነት በመጠቀም በኃይል የሥርዓት ለውጥ ለማምጣት ያደረገው ሙከራ

ከሽፎበታል፡፡ እንዲሁም  ህገመንግሥታዊ ሥርዓቱን በኃይል የማፍረስ ዓላማና ተልዕኮን ከዳር ለማድረስ ጀምሮት የነበረው እንቅስቃሴ በቀላሉ የሚታይ አይደለም፡፡

የዚሁ የቀድሞው ቅንጅት ከፍተኛ አመራር የነበሩት ዶ/ር ብርሀኑ ነጋና አንዳንድ ዋና ዋና ተባባሪዎቻቸው ከተቀሩት አመራሮች ተለይተው ወደ ውጪ ኮብልለው የሥርዓት ለውጥ ለማምጣት ተደራጅተው በይፋ የትጥቅ ትግል ማወጃቸውም ለዚሁ ፀረዲሞክራሲ አቋማቸው ማረጋገጫ ነው፡፡

ይህ የጦርነት ምርጫቸው በሀገሪቱ ተደራጅቶ ለመታገል የሚያስችል ዲሞክራሲና የመደራጀት መብት ጠፍቶ ወይም በህገመንግሥቱ ሳይደገፍ ቀርቶ ሳይሆን ከባህሪያቸው የመነጨ መንግሥታዊ አቋማቸው ነፀብራቅ ነው፡፡

በአሁኑ ሰዓት የኢትዮጵያ ህዝብ የህገ መንግሥቱና የመንግሥት ሥልጣን ባለቤትና ምንጭ መሆኑን ከመቼውም ጊዜ በላይ ተገንዝቧል፡፡ በሂደትም ተቃዋሚ ፓርቲዎች ህገ መንግሥታዊ ባልሆነ ሥልት የሥርዓት ለውጥ  የማምጣት ዝንባሌ ያላቸው መሆኑንም ተረድቷል፡፡ የማህበረሰብ እድገትና የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ እውን የሚሆነው ህዝቡ ራሱ በየወቅቱ የተደረሰበትን ዕድገት ቀጣይነት በማረጋገጥ ብቻ የመሆኑ እውነታም በአሁኑ ወቅት ከህዝቡ የተሰወረ አይደለም፡፡ በሌላ አነጋገር የተደረሰበትን የእድገት ደረጃ እያፈረሱ ከዜሮ የመጀመር የዜሮ ድምር ጨዋታ የትም እንደማያደርስ ያውቃል፡፡

በነዚህና መሰል ምክንያቶች ነው ህዝቡ በዘንድሮው ምርጫ ለዘብተኛ አቋም ያላቸውን ፅንፈኛ ተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎች በተመሳሳይ ሁኔታ ድምፁን የነፈጋቸውና የሥርዓቱን ቀጣይነት በድምፁ ያረጋገጠው፡፡

ተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎች በህገ መንግሥቱ አንቀጾች ላይ ያላቸውን የከረረ ተቃውሞ የምርጫ አጀንዳቸው በማድረግ የሥርዓት ለውጥ ለማምጣት ይዘውት የነበረው አቋም የህዝብን ድምፅ ሊያስገኝላቸው እንዳልቻለና ወደፊትም ቢሆን እንደማይችል በግልጽ ሊረዱት ይገባል፡፡ በአጠቃላይ በዘንድሮው አራተኛ ዙር አገራዊ ምርጫ ላይ በገዥው ፓርቲ በሰፊ የድምፅ ልዩነት ለመሸነፍ ያበቃቸው ዋነኛው ምክንያትም ይኸው ከላይ የተዘረዘረው ህገመንግሥታዊ ሥርዓቱን የመለወጥ የተሳሳተ አካሄዳቸው ነው፡፡

በዘንድሮው ምርጫ ያገኙት ድምፅ የም/ቤት መቀመጫ ለማግኘት አላስቻላቸውም፡፡በመሆኑም ለሽንፈታቸው መሸፈኛ የተለያዩ አስተያየቶችን በማቅረብ ላይ ናቸው፡፡ በምርጫው ሂደትና ወቅት ሲያቀርቡት የቆዩት፣ በአባሎቻችን ላይ እስር፣ ድብደባ፣ ወከባ... ተፈፀመ›› የሚለውን ዓይነት ሀሰተኛ ውንጀላ፣ ከምርጫው በኋላም ‹‹ምርጫው ተጭበርብሯል››፣‹‹የመድበለ ፓርቲ ሥርዓት በኢትዮጵያ አብቅቶለታል›› እና ‹‹በአዲስ መልክ ሥራ ጀምረናል ›› የሚል ዓይነት የማስታወቂያ ስም ጋር የሚመሳሰል ክስ እያስደመጡን ያሉት፡፡ የመድረክ አመራር የሆኑት አቶ ስዬ አብርሀ በቅርቡ ከጀርመን ድምፅ ሬዲዮ የአማርኛ ፕሮግራም ጋር ባደረጉት ቃለ ምልልስ ያቀረቡት ሀሳብም የዚሁ ሽንፈትን ላለመቀበል የሚደረግ‹‹ክስ›› አካል ነው፡፡

በመሰረቱ በአንድ አገር የፖለቲካ ህይወት ውስጥ‹‹የመድበለ ፓርቲ ሥርዓት አለ ወይንስ የለም?›› የሚለው ጉዳይ የሚወሰነው በዘንድሮው ምርጫ እንደታየው አንድ ፓርቲ እጅግ ሰፊ በሆነ የድምፅ ልዩነት አሸንፎ ሥልጣን የሚረከብበት ሁኔታ በመኖሩ ወይም ባለመኖሩ ብቻ አይደለም፡፡ የዚህ ዓይነት የምርጫ ውጤት በኢትዮጵያ ብቻ የታየ ልዩና አዲስ የታሪክ ክስተትም አይደለም፡፡ በሌሎች የመድበለ ፓርቲ ሥርዓት በሚከተሉ አገሮችም ታይቷል፡፡

በዚሁ በያዝነው ዓመት እንኳ በዶሚኒካ ሪፐብሊክ በተካሄደ ምርጫ የዶሚኒካ ሠራተኞች ፓርቲ ከ21 የምክር ቤት መቀመጫዎች 18ቱን ሲያሸንፍ፣ 3ቱን ተቃዋሚው የተባበሩት ሠራተኞች ፓርቲ አግኝቷል፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ በሲንጋፖር በተካሄደ ምርጫም ሀገሪቱ ከቅኝ ግዛት ከወጣችበት ጊዜ ጀምሮ ሥልጣን ላይ የቆየው አክሽን ፓርቲ ከ84 የም/ቤት መቀመጫዎች 82ቱን በማግኘት አሸናፊ ለመሆን በቅቷል፡፡

የመድበለ ፓርቲ ሥርዓት መኖር አለመኖር መሠረታዊ መገለጫ ዜጎች ባመኑበት የፖለቲካ አመለካከት አንድ ፖለቲካ ፓርቲ አደራጅተው ህጋዊ እውቅና ተሰጥቷቸው፣ አቋማቸውንና አመለካከታቸውን በይፋ የማራመድ፣ ለመንግሥት ሥልጣን የመፎካከር መብታቸው በህገመንግሥት የተረጋገጠ መሆኑ ወይም አለመሆኑ ነው፡፡ የኢትዮጵያ ተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎች በዘንድሮው ምርጫ የምክር ቤት መቀመጫ ለማግኘት የሚያስችል ድምፅ ማጣታቸው/በህዝቡ አለመመረጣቸው/ እነዚህን በህገመንግሥቱ የተረጋገጡ መብቶቻቸውን እና ነፃነታቸውን አላሳጣቸውም፡፡ የህዝቡን ፍላጎትና ጥቅም ያገናዘበ አቋምና ፖሊሲ ይዘው ከቀረቡ፣ በቀጣዩ ምርጫ የተሻለ ስኬት ወይም የማሸነፍ ዕድል ሊያገኙ ይችላሉ፡፡ ዕድሉ በእራሳቸው እጅ ውስጥ ነው ያለው፡፡

‹‹ህዝቡ እንዴት አንድ ፓርቲ እንዲኖር ሊመርጥ ይችላል? ይሄ ቧልት ነው›› የሚለውን የአቶ ስዬ አስተያየት ከምርጫው ሂደትና ውጤት ጋር አያይዘን ስናየው ትርጉም አልባ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ ህጋዊ ሆነው የሚንቀሳቀሱ የፖለቲካ ፓርቲዎች ሁሉ ባላቸው በህዝብ ድምፅ የመመረጥ እኩል ህገ መንግሥታዊ መብት መሠረት በውድድር ቀርበው ህዝቡ ከእነዚህ ውስጥ አንድን ፓርቲ በአብላጫ ድምፅ መረጠ እንጂ አገሪቱ አንድ ፓርቲ ብቻ ይኑራት ብሎ አልመረጠም ወይም አልወሰነም፡፡

በአጠቃላይ ይነስም ይብዛ ተወዳዳሪ ፓርቲዎች ሁሉ የየራሳቸውን የህዝብ ድምፅ አግኝተዋል፡፡ የአብዛኛውን መራጭ ድምፅ ማግኘት አለማግኘት ግን ሌላ ጉዳይ ነው፡፡ ለሽንፈታቸው ሌላ ሰበብ ከመፈለግ፣ ካሉበት የፖለቲካም ይሁን የቁም ቅዠት በአስቸኳይ ወጥተው ነባራዊውን ዓለም ቢመለከቱ የበለጠ ያዘልቃቸዋል፡፡